# ግልጽ ደብዳቤ ለአውሮፓ ስፖረትና ባህል ፌዴሬሽን

ታህሳስ 6 ቀን 2003 ዓ. ም. (15 ድሴምበር 2010)

በቅድሚያ ለፌደሬሽኑ አመራር አባላት እንዲሁም በአውሮፓ ለውድድር ተሳታፊነት ለሚሰበሰቡ የያገራቱ ቡድኖች ሁሉ የእንግሊዝ ኢትዮ ስታር ሎንዶን ቡድን ሰላምታችንን በአክብሮት እንገልጻለን። በማስከተልም ከዚህ በታች በምናቀርበው ፅሁፋችን ላይ ግልፅና ቀጥተኛ የሆነ አመለካከትና እንዲሁም ለተከሰቱት ምክንያቶችና ለተደረጉት ጥረቶች ከበቂ መረጃ ጋር በሙሉ በዚህ ፅሁፋችን ላይ ለማስፈር ግድ ይለናል።

እንደሚታወሰው ባለፉት ወራቶች ጀምሮ እስካሁን ድረስ ወሬውና ድርጊቱ አእምሮአችንን እረፍት እየነሳ ያለውን የ9ኛውን የአውሮፓ ስፖርት በአል ውድድር የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን በተካተተበት በአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌደረሽንና በዚሁ ፌደሬሽን በታቀፉት ክለቦች ምርጫ በብርታኒያ እንዲዘጋጅ የተፈቀደውን ውሳኔ የእንግሊዝ ኢትዮ ስታር ሎንደን በደብዳቤ ውድድሩን የማያዘጋጅ መሆኑን ገለፀ ስለተባለው ዝርዝር አንድ በአንድ እንደሚከተለው እንገልፃለን።

እንደሚታወቀው የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን በአውሮፓ ስፖርት ባህል ፌደሬሽን ከመስራቾቹ በቀዳሚነት አንዱ የሆነና እንዲሁም ከአመት አመት በሚደረጉት ውድድሮች በበለጠ ዝግጅት ተሳትፎና ለአውሮፓ ኢትዮጵያዊያን ስፖርት መዳበር፣ ብሎም ተበታትኖ ያለውን ኢትዮጵያውያን ለማገናኘት ለሚደረገው ጥረት ለማሳካት የበኩላችንን አስተዋፅዎ ያደረገና እያደረግንም ያለን መሆናችን ግልፅ ነው። ሆኖም ባለፈው እ. ኤ. አ. በ23/10/2010 የአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌደሬሽን ያወጣውን መግለጫ ተመልክተናል። በተጨማሪም በመግለጫው ላይ ኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን 9ኛውን የአውሮፓ እግር ኳስ ውድድር ፕሮግራም እንደማያዘጋጅ በፅሁፍ ገለፀ ተብሎ በድህረ ገፅ ላይ የሰፈረውን እንደ ማንኛውም ግለሰብ አይተንና አንብበን ከመገረማችን አልፎ በሁኔታው 99% የሚሆኑትን የኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድንን እጅግ ቅር ያሰኘ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ድርጊት ሁሉ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የቡድኑ ዋና ዋና (ኮር) መስራቾች ችግሮቻችንን ለመፍታት በማሰብ የየበኩላችንን ጥረት በተለያየ መንገድ በመጀመራችንና የአሰብናቸውን እቅዶች ለማሳካት ስንል በወቅቱ በድረ-ገፅ ለወጣው መግለጫ መልስ ለመስጠት አለመቻላችን ምናልባትም ሌላ ግምት ውስጥ ያስገባናል ብለን እናምናለን።

የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን ካለው ረጅም አመት ታሪክ አብሮ ከመኖር አልፎ ከወንድማማችነት ፍቅር የተነሳ አብዛኛው ነባርና እውቅ መስራች ተጫዋቾች ባልተማከሩበት ሁኔታ፣ ጥቅማዊ እቅድ በመፈፀም፣ በአልተስተዋለ ድርጊት በመነሳት፣ መላው ኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን አባላት በማያውቁትና በአልተገኙበት ስብሰባ፣ ሁለቱ የቡድኑ አመራር ግለሰቦች እንዲሆኑ ብለን ያስቀመጥናቸውና ያጠቃላይ የቡድኑን አባሎች ሀሳብና ፍላጎት ያንፀባርቁልናል ብለን ከቅርብ አመታት ወዲህ በልባዊ እምነት የምንጠብቃቸው አቶ ዮሐንስ መሰለና አቶ አበበ ቶለሳ ከሚፈልጓቸው

ጥቂት ግለሰቦች ጋር በመሆን፣ ለጥቅማዊ ድርጊታቸው ለፃፉት ደብባቤ ምንም አይነት ግንዛቤና እውቅና የሌለን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ለንደን ቡድን እስከ 8ኛው አመት የአውሮፓ ውድድር ሲካፈል ከዚህ በፊት በሌሎች አውሮፓ አገሮች ዝግጅት እንዲደረግና ምናልባትም ቀደም ባሉት አመታት የውድድሩን ዝግጅት ለማዘጋጀት ያልፈቀደበት ምክኒያት የአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌደሬሽን በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቆይና በተለያዩ የአውሮፓ አገራት እግር ኳስ ቡድኖች ምናልባትም በጉዞ ወደ እንግሊዝ ለንደን የመምጣቱ ሁኔታ ያስቸግራቸዋል ብሎ በማሰብና የማስተናገዱ ተራ እንዲደርሳቸው ለሚጠይቁ ተወዳዳሪ ቡድኖቹም ፍላጎታችንን አሳልፈን መስጠታችን በነበረን በጎ አመለካከት ነበር። ታዲያ ይሄንን ሁሉ አመታት ካሳለፍን በሁዋላ ላብዛኛው የአውሮፓ የእግር ኳስ ተወዳዳሪ ቡድን በአሁኑ ግዜ ሁኔታዎች ተመቻችተው በፈቀደበት ሰአት የ9ኛውን የአውሮፓ የእግር ኳስ ቡድን ውድድር ፕሮግራም ዝግጅት ቡድናችን ለማዘጋጀት በታላቅ ፍላጎትና ጉጉት ያገኘውን እድል "በውስጣዊ አሰራር አለመግባባትና መጓተት" በሚል ርዕስ እነኚሁ ከላይ የጠቀስናቸው ግለሰቦች የሃሰት ፅሁፍ በድረ ገፅ ላይ በማስፈርና የግል ጥቅም ፍላጎታቸውን ከተወሰኑ እውቅና ከሌላቸው የቡድኑ ግለሰቦች ጋር በጎን ገንዘብ በማዋጣት፣ ከዛም ሁኔታውን እንደፈለጉት ለማድረግ አለመቻላቸውን ሲረዱ የአብዛኛው የኢትዮ-ስታር ቡድን አባል ውሳኔ በማስመሰል በአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌደሬሽን ውስጥ ባላቸው የውክልና አመራርና ስልጣን በመጠቀም እንዲመለስ አድርገዋል።

ዛሬ የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ለንደን ቡድን በእግር ኳስ ብቃት ያላቸው ተጫዋቾች የሚገኙበትና በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ የተጫወቱ ተጫዋቾችን ያካተተና በተጨማሪም ከሌላው አውሮፓ አገሮች በበለጠ ብዙ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩባት እንግሊዝ አገር ከመሆኑዋ ባሻገር ይህን ያገኘነውን የ9ኛውን የአውሮፓ እግር ኳስ ውድድር በለንደን እንዲዘጋጅ ፍላጎት የነበረው የኢትዮ-ስታር ለንደን ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ የስፖርት ቤተሰቦችና በእንግሊዝ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲና ሕብረተሰቡ ሆኖ ሳለ የዝግጅቱን ፕሮግራም ግለሰቦቹ በማሰናከል ምናልባትም ቀናና በጎ አመለካከት ሳይኖራቸው አላማውን ካለመገንዘብ በአንድ አቅጣጫ ብቻ በማሰብ ሌላ አማራጭ የሚሆን ሐሳብ ሳይፈለግ የተገኘውን ዝግጅት በመመለስ ምን አይነት ምክኒያት ነው ሊባል ይችላል። ስለዚህም አቶ ዮሐንስና አቶ አበበ የኢትዮ-ስታር ለንደን የቡድኑን ሐሳብ አጠቃላይ በደብዳቤ በድረ ገፅ ላይ ገልፀናል ብለው ለተፃፉት ሐተታ ግለሰቦቹ ተጠያቂዎች መሆናቸውንና ይህም ጉዳይ የአብላጫው (የብዙሃኑ) የቡድኑ አባላት ሐሳብና ውሳኔ እንዳልሆነ በጥብቅ ለማሳሰብ እንወዳለን። እስካሁንም አብላጫው የቡድኑ አባላት መልስ ያልሰጠበት ዋናው ምክንያት ለረጅም አመት በወንድማማችነት አብሮ ተከባብረን በመኖርና ብሎም የአንድ ትውልድ ዜጎች መሆናችንን በመገንዘብና ጨዋነትን ግምት ውስጥ በማስገባት ጉዳያችን እልባት እንዲያገኝ በለንደን ከተማ የተለያየ የሙያ ብቃት ባላቸው በእድሜም ጠና ባሉ ባገራችን ባሕል ተመክሮ በሽምግልና መልክ የመግባባትና የማስታረቅ ክንዋኔን በተሰጠበትና ለጉዳያችን መፍትሄ እንዲገኝለት ስንል በወቅቱ መልስ ለመስጠት ዘገየን። የሚገርመውና በጣም የሚያስደነግጠው ከሽማግሌዎቹ ጋር

የሃይማኖት አባታችንን በሁኔታችን ውስጥ በማስገባት ለማግባባት ጥረት ከተደረገ በሁዋላ በመጨረሻ አንድ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ባማራጭ ለማግባቢያ እንዲመች የኢትዮ-ስታር የቡድኑ አባላት በተገኙበት የውድድር ዝግጅት በድምፅ ብልጫ ይወሰን በሚል ትልቅ ስብሰባ ተካሂዶ ነበር። ታዲያ ይህ ስብሰባ በመላው የቡድኑ አባላት በተደገፈ ታላቅ የውሳኔ መፍትሄ ካመጣ በሁዋላ ውድድሩን እንግሊዝ ሎንደን ለማምጣት ለመላው አባላት በክርስቲያን ሃይማኖታችን ስም አቶ ዮሐንስና አቶ አበበ ቃል በመግባት ወደ አውሮፓ ለስብሰባ በተገኙበት ላይ ባላቸው የአውሮፓ የፌደሬሽኑ የስራ አመራር ሃላፊነት ለኢትዮ-ስታር ሎንደን የተሰጠውን የእግር ኳስ ውድድር ዝግጅት ፕሮግራም በማስተባበር እንደሚመልሱና ዝግጅቱን ከመላው በእንግሊዝ ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ ሕብረተሰብ ጋር ለማዘጋጀት ቃል የተገባበት ፍላጎት ሃሳብንና ስሜትን የሚገልፅ ድምፅ ይዘው እንዲሄዱ ከተማከርን በሁዋላ የአውሮፓ ስፖርት ባሕል ፌደሬሽን በሆላንድ አምስተርዳም የአመራር ዝግ ስብሰባ ላይ ግለሰቦቹ ዝግጅቱን ማካሄድ እንደማንችልና ወደ እንግሊዝ ከመመለሳቸው በፊት የሃሰት መግለጫ ውሳኔው እንደማይቀየር በድረ ገፅ ከገልፁ  በሁዋላ ሲመለሱ በሎንደን ተቀጣይ የጉጉት ስብሰባችን ላይ በመገኘት ለሽማግሌዎችና ለኢትዮ-ስታር ቡድን አባለት በተሰበሰቡበት ያመጣነውን የክልክል ውሳኔ እንግሊዝ ለሚገኘው ሕብረተሰብ መግለጫ ይሰጥልን ብለው ግለሰቦቹ ሃሳብ አቅርበው የሚገርም ትርኢታዊ ድርጊት ነበር። እንግዲህ ከላይ ለወጣብን መግለጫ መልስ ከሞላ ጎደል ለመስጠት ብንሞክርም ወደፊት በረቀቀ በስፋት የኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድንና አባላቱ ምን እንደሚመስል በተለየ መልኩ በዝርዝር እስክናስቀምጥ ድረስ የሚከተለውን ውሳኔ ወስነናል።

1. የ9ኛው የአውሮፓ የእግር ኳስ ውድድር በማረጋገጫ እንዲያዘጋጅ ዋስትና ለተሰጠው ለእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ሎንደን ያለምንም ቅድመ እቅድ እንዲመለስ፣

2. አቶ ዮሐንስ መሰለና አቶ አበበ ቶሎሳ የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ቡድን እንደማንኛውም አባል እንጂ ቡድኑን በተወካይነትም ሆነ በሃላፊነት የማይወክሉ መሁናቸውን፣

3. በምትካቸው የሰየምናቸው የኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን አባላት በፅሁፍ በሚሰጣቸው የተረጋገጠ እውቅና በግዚያዊ ተወካይነትና በሐላፊነት የሚመሩ ግለሰቦች መርጠን ከወዲሁ ስላደረግን በማንኛውም በአውሮፓ የስብሰባ ጉዳዮች ላይ ስለቡድናችን ባለው ሁኔታ ሁሉ በአካል በመገኘት እንደሚሳተፉ ከወዲሁ እናሳስበለን።

ስለዚሕም ከላይ በግልፅ ያተትነውን እውነታ የአውሮፓው ፌደሬሽን በመገንዘብ እና ከግምት በማሰገባት የስፖርት ዝግጅቱን እንዲናዘጋጅ በማድረግ የቡድናችንን፣ በአጠቃላይም በብሪታያ የሚኖሩትን መላው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት እቅድና ጉጉት እውን ለማድረግ እንደማያዳግተው ሙሉ እምነት አለን።

በመጨረሻም ለወዳጅ ኢትዮጵያዊ ሕብረተሰባችን ልናስታውሳችሁ የምንወደው በወጣው መግለጫ ላይ “ሓላፊነት ከሸክም ይከብዳል” ተብሎ ከተጠቀሰው የሓላፊነት ትንሽ የለውም ከሚለው በመነሳት እኛም የበኩላችንን እንዲህ እንላለን። በቅን ላሰብን ሰዎች

የሚያሳዝነንና ሊያስቆጣን የሚገባው ነገር እነዚህ ሁለቱ ግለሰቦች ሊያስመሰግናቸውና ሊያስከብራቸው የሚችለውን የኢትዮ-ስታር ሎንደን ቡድን እድልና ቡድናችን በአውሮፓ ያለውን ትልቅነት ክብርና በቀጳሚ መስራችነት መሰረት በመነሳት ቡድናችንን በማደስና በማጠናከር የምንገነባበትን ታሪካዊ አጋጣሚ እንደተራ ቀላል ነገር በመቁጠር በማሕላችን ጥቁር ነጥብ ጥለው ዝግጅቱ እንዳይካሄድ በማስደረጋቸውና በዚሁ ጉዳይ አብረው ለተባበሩዋቸው ጥቂት ግለሰቦች ጋር እኛንም አጠቃለው ባንድ ስም ማፈሪያ ከመሆን አለማምለጣችን ከልብ አሳዝኖናል። ሆኖም የኛ ምክር በአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌደሬሽን ውስጥ የስልጣን ጥቅመኞችንና የግል ፍላጎትን ለማርካት ከሚጣደፉ አመራር አባላት (ስልጣኑን በአግባቡ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት ሊያውሉት ሌተቀን ከሚለፉትና በጠቅላላው አመራሩን ሚዛናዊ ፍርድ እንዳይኖረውና ሕጉን ተከትሎ እንዳይሄድ ከሚያዘናጉ) ግለሰቦችን ለይቶ የሚመለከትበት የግንዛቤ ደንብ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ስለዚህም በተለይ ትልቅ ሃላፊነትንና ተጠያቂነትን ሊያስጠይቅ የሚችልን የአመራር ቦታ በአግባቡ የተሰጣቸውን ሃላፊነት ባላደራነታቸውን የሚገነዘቡና እንዲሁም የስፖርቱ መላው ቤተሰብን ጥቅምና ፍላጎት ዋና አላማቸው ሊያደርጉ መሆን ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ፌደረሽኑ ከሚያስበውና ከሚያልመው አላማና ግብ ለመድረስ ያዳግተዋል በማለት አስተያየታችንን እንገልፃለን።

የእንግሊዝ ኢትዮ-ስታር ሎንደን እግር ኳስ ቡድን<br>ታህሳስ 6 ቀን 2003 ዓ. ም.